የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 45
ADDIS ABABA 3rd July, 2013


ማውጫ

CONTENTS


አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፬/፪ሺ፭ ዓ.ም

በውጤት ላይ ለተመሠረተ የምዕተ ዓመቱ የጤና ግቦች ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ..........ገጽ ፮ሺ፰፻፺፯

**Proclamation No. 794/2013**

**International Development Association Financing Agreement for the Financing of Health Millennium Development Goals Program for Results Ratification Proclamation .... Page 6897**


## አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፬/፪ሺ፭

## <u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

በውጤት ላይ ለተመሰረተ የምዕተ ዓመቱ የጤና ግቦች ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፷፭ ሚሊዮን ፩፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. (ስልሳ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ስፔሻል ድሮዊንግ ራይትስ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ማርች ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፬ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 794/2013

## <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION</u>

WHEREAS, Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 65,100,000 SDR (sixty five million one hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Health Millennium Development Goals Program for Results was signed in Addis Ababa on the 29th day of March, 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 11th day of June, 2013;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:


ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30



www.chilot.me

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በውጤት ላይ ለተመሠረተ የምዕተ ዓመቱ የጤና ግቦች ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፬/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ማርች ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5209-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፷፭ ሚሊዮን ፩፻ሺ ኤስ.ዲ.አር. (ስልሳ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ስፔሻል ድሮዊንግ ራይትስ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Financing of Health Millennium Development Goals Program for Results Ratification Proclamation No. 794/2013".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit Number 5209-ET signed in Addis Ababa on the 29th day of March, 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 65,100,000 SDR (sixty five million one hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of July, 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

www.chilot.me